በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ከጁላይ 1-10/2025 የነበረዉ የአየር ሁኔታ ግምግማ እንዲሁም ከጁላይ 11-21 እና ከጁላይ 21-31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁላይ 2025

አዲስ አበባ

1.1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ጠባይ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በ 24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል ባህርዳር 34፣ 62.3፣ ጎንደር 35.5፣ 39.7፣ ጎሬ 39.5፣ ጅማ 39.7፣ መተሃራ 40፣ ነቀምት 58.1፣ አቦምሳ 52.5፣ አዴት 36፣ አማን 43.6፣ 65.6፣ አንግር ጉትን 30.2፣ አርጆ 34፣ አይከል 32.5፣ 31.4፣ ቡለን 39፣ ዳንግላ 39.7፣ ደብረ ብርሃን 35.5፣ ደብረ ታቦር 30.4፣ 52.7፣ ኢጃጂ 30.8፣ እነዋሪ 36.3፣ ፊኙንዶ 30.6፣ 64.5፣ ጋምቤላ 38.5፣ 39.2፣ 33.7፣ ወሊሶ 35.9፣ 43.6፣ ጊምቢ 58.3፣ ጉንዶ መስቀል 36፣ 32.8፣ ሊሙገነት 101፣ ማሻ 30.2፣ 40.4፣ 50.2፣ መተማ 37.4፣ ሞጣ 31.7፣ 32.1፣ አዳማ 71.3፣ ንፋስ መዉጪያ 32.8፣ 36.8፣ ፓዌ 31.5፣ ሰኮሩ 64.6፣ ሻምቡ 38.8፣ ተርጫ 45.6፣ ወረኢሉ 39.1፣ ወላይታ 44.1፣ የትኖራ 47.3፣ 57.7፣ አሳሳ 30.5፣ አዋሮ መልካ 55.4፣ ፊስ ቤት 35.9፣ጋሸና 37.2፣ ሃሮ 30.2፣ 30.4፣ 40፣ 30.2፣ ቢላምቢሎ 63.7፣ ደራ 40.5፣ ዲንሾ 45.2፣ መንደዲ 64.8፣ 65.5፣114.8፣ ሰቆጣ 30.5፣ ቅዳሜ ገበያ 56.7 እንዲሁም ኩሚ 80.4፣ ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፈዉ የጁላይ የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በ54 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በምዕራብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 50.2 እስከ 114.8 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል መንደዲ፣ ሊሙ ገነት፣ ኩሚ፣ አማን፣ ሰኮሩ፤ ፉኙንዶ፣ ባህር ዳር ፣ ጊምቢ፣ ነቀምት፣ የትኖራ፣ ቅዳሜ ገበያ፣ ደብረ ታቦር፣ አቦምሳ፣ ማሻ፣ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et



ምስል፡1 ከጁላይ 1-10 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፉት የጁላይ አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ የመካከለኛዉ፣ የምዕራብና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ የሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኙዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ወላይታና ባስኬቶ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ ከ51-350 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡



ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ባለፉት የጁላይ አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር፤ ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ፣ ምስራቅ ቦረና፣ መዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብና ምስራቅ ሸዋ፣ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ የመካከለኛዉ፣ የምዕራብና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ የሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ከአፋር ክልል ቀልበቲ፣ ፋንቲ፣ ሃ እና ጋቢ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ወላይታና ባስኬቶ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር

በሌላ በኩል በኤሊዳር፣ ሰመራ፣ አዋሽ አርባ፣ አይሻ፣ ገዋኔ፣ መተሃራ፣ ጭፍራ፣ ሸዋ ሮቢት፣ ድሬ ዳዋ፣ ቀበሪዳሀር፣ ጨፋ፣ መተማ፣ ኑራ ኤራ፣ ጎዴ፣ ባቲ፣ ፉኙዶ፣ ጋምቤላ፣ መኤሶ፣ ማሻ፣ አቦምሳ፣ ላሬ፣ አቦቦ፣ ሽርቀሌ፣ ስሪንቃ፣ ኮምቦልቻ፣ ጅግጅጋ እና አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 31.0 እስከ 45.8 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል፡፡

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

1.2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በተለይም ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት በአብዛኛው የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች ላይ እንደነበራቸው የተሰበሰቡና የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም የተገኘዉ እርጥበት ከጁላይ ጀምሮ ለሚዘሩ የተለያዩ የመካከለኛ ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራትና ከኤፕሪል ጀምሮ ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ያሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር የጎላ አስተዋፅዖ ነበረዉ። በተጨማሪም በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው እርጥበት የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ ምንጮችን ከማጎልበቱም በላይ የተሻለ የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት እንዲኖር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድ ዝናብ እንድሁም ባሳለፍናቸው ቀናት በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በነበሩ ቦታዎች የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት እና በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የወንዝ መሙላትና የጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የጎርፍ መከሰት የነበረ ቢሆንም፤ በግብርናዉ አንቅስቃሴ ላይ ያደረሰዉ የጎላ አሉታዊ ተፅዕኖ አልነበረም (ካርታ 4)።



ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

1.3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

ባሳለፍነው የጁላይ የመጀመርያው አስር ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ተከዜ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛው፣ መካከለኛው እንዲሁም ታችኛው አዋሽ የወሎ ተራራ አዋሳኝ ተፋሰስ፣ በላይኛው ዋቢ ሸበሌ እና በጥቂት ላይኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት ነበራቸው፡፡በተጨማሪም በላይኛው እና መካከለኛው አባይ፣ መካከለኛው ኦሞ ጊቤ እና በላይኛው ባሮ አኮቦ እንዲሁም በጥቂት ላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ለገፀ ምድር ውሃ መሻሻል ጥሩ አስተዋፅዖ እንደ ነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚትዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 5)፡፡



ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በጁን ወር ውስጥ የተቀሩትን የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ሙሉ በሙሉ ያዳርሳል፡፡ በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ወር የክረምት ዝናብ በብዙ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋ እና እየተጠናከረ የሚሄድበት ጊዜ ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የተሻለ ዝናብ መጠንና ስርጭት ይስተዋላል። በወሩ በመደበኛው ሁኔታ የሚጠበቀው አማካይ የዝናብ መጠን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ ስፍራዎች ላይ ከ200-500 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ18-27 ቀናት ያህል ይዘንባል። በሌላ በኩል በመካከለኛው፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን ከ60-200ሚ.ሜ የሚደረስ ዝናብ ከ6-21 ቀናት ያህል ይዘንባል፡፡ ከክረምት ወቅት ዝናብ ድርሻ አኳያ በጁላይ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ከ30 እስከ 50% የሚሆነውን የወቅቱን የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ።

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ሁለተኛ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ይበልጥ ይጠናከራሉ፡፡ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን እና መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ነጎድጓዳማ እና ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይዘወተራል፡፡

2.1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በጁላይ ሁለተኛ አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ይበልጥ እየተስፋፉና እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛው፣ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)። ስለሆነም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅና በምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡በሌላ በኩል በሰሜን ምስራቅ፤ መካከለኛው እና ምዕራብ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡



ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 11-20, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን

2.2 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

በሚቀጥሉት ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከመካከለኛ እስከ ከባድ (ከ1-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7) ፡፡



ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 11-20, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት ቀናቶች ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና የሚያገኙት የዝናብ መጠን

ክልል	ዞን	በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን
አሮሚያ	የምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች	ከባድ መጠን (ከ30 ሚ.ሜ በላይ)
	የምዕራብ አርሲ እና አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
	የምስራቅ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ቦረና ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)
አማራ	የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም ዞኖች	ከባድ መጠን (ከ30 ሚ.ሜ በላይ)

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

	የዋግ ህምራ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ትግራይ	የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ ትግራይ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
	የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ)
ቤንሻንጉል ጉምዝ	የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ጋምቤላ	የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ)
ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ	የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣	ከባድ መጠን (ከ30 ሚ.ሜ በላይ)
	ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ማዕከላዊ ኢትዮጵያ	ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ሲዳማ ክልል	ሁሉም የክልሉ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ		ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
አፋር	የማሂ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

	የቀልበቲ፣ ፊንቲ፣ አውሲ፣	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ)
ደቡብ ኢትዮጵያ	የወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ባስኬቶ እና ጌድዮ፣	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
	አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ)
ሶማሌ	ሲቲ፣ ፋፈን፣ ኤረር፣	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ)
	የጀረር፣ ነጎብ፣ ቆራሂ እና ዳዋ፣ ዞኖች	ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ)

2.3 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በጁላይ የሁለተኛው አስር ቀናት ከሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ በተለይም የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በኤሊ ዳር፣ ዱብቲ፣ ሰመራ፣ ቡሬ፣ አሳይታ፣ ሁንዱፎ፣ ገዋኔ፣ ሚሌ፣ ዳሊፋጊ፣ አይሻ፣ ጉሊና፣ አዋሽ አርባ፣ ባቲ፣ ዶሎ ኦዶ፣ ዳዋ፣ ጎዴ፣ አቦቦ፣ ቋራ፣ አዋሽ ፊንታሌ፣ ጭፍራ፣ ላሬ፣ መተሃራ እና ፉኙዶ አከባበዎች ላይ ከ30.2 እስከ 41 ዲግሪ ሴልሺየስ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8)፡፡



ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 11-20, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

2.4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ሦስተኛው አሥራ አንድ ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎችን ይበልጥ የሚጠናከሩ ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን እና መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ነጎድጓዳማ እና ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይዘወተራል፡፡

በመጪዎቹ የጁላይ ሦስተኛው አሥራ አንድ ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር በተያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን እና መካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የአሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

2.5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን እንድሁም ሰሜን ምስራቅ፣ ምስራቅና መካከለኛዉ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ይኖራቸዋል። ይህም የሚጠበቀው እርጥበት ለወቅቱ የግብርና ስራ እንቅሥቃሴ በአመዛኙ አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ቢሆንም፤ ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

Ethiopian Meteorology Institute

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

ዞኖች	የእርጥበት ሁኔታ	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የተሰጠ ምክረ ሃሳብ
የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የመኸር አምራች ዞኖች				
ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ ዞኖች፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም ዞኖች፣ዋግ ህምራ፣ ሰሜን እና የደቡብ ወሎ፣ሰሜን ሸዋ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ ትግራይ ዞኖች፣ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ፣ አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ ፣ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካና ምዕራብ ኦሞ	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት	• የአፈር ወስጥ የእርጥበት መጠን መሻሻል • ለረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት በቂ እርጥበት መኖር • ከሐምሌ ጀምሮ ለሚዘሩ ሰብሎች በቂ እርጥበት መኖር • የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል	• በእረሻ ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት • ውሃ ገብ በሆኑና አካባቢዎች የአፈር መታጠብ • የአረም መስፋፋት • ሸክላማ አፈር ማሳዎች መጨቀየት	• በሚኖረው እርጥበት ዘር መዝራት • ትርፍ ውሃን ከማሳ በማንጣፈፍ ማስወገድ • የአፈር መሸርሸር ሳጋትን ለመቀነስ ጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት • የማዳበሪያ አጠቃቀምን በትክክለኛው ሰዓት መተግበር • አረምን በወቅቱ ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበር
የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ቀልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ፣ ማሂ፣ ሀሪና ጋቢ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት	• ለመኸር እርሻ ስራ እንቅስቃሴ ለማከናወን • ለረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገት • የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት መሻሻል • ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት	• ከፍተኛ ትነትና ዝቅተኛ የአፈር እርጥበት •	• የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም የማሳ ዝግጅትና ዘር ማከናወን • የእርጥበት እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የአፈርና የውሃ እቀባ ስራ ማከናወን • የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውና የመኸር አብቃይ የሆኑ ዞኖች				
የሲዳማ ሁሉም የክልሉ ዞኖች፣ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ባስኬቶ፣ ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ ምዕራብ አርሲ፣አርሲ እና ምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት	• ቀድመው ለተዘሩ ለረጅም ጊዜ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት • ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት • የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማጠራቀም	• ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውሃ በማሳዎች ላይ መተኛት • የደረሱ የበልግ ሰብሎች በእርጥበት መጎዳት	• ረባዳማ በሆኑ ማሳዎች የውሃ ማንጣፈፍ ስራዎችን መስራት • የደረሱ የበልግ ሰብሎችን በሚኖሩ ደረቅ ቀናቶች መሰብሰብ
ባሌ፣ ምስራቅ ባሌና የምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት	• ለመኸር ሰብሎችን ዘር የመዝራት ስራ ለማከናወን • ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል	• ከፍተኛ ትነት መኖር • የደረሱ የበልግ ሰብሎች በእርጥበት መጎዳት	• የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም የመኸር የዘር መዝራት ማከናወን • የደረሱ የበልግ ሰብሎችን የሚኖሩ ደረቅ ቀናቶች በመጠቀም መሰብሰብ
በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች				
ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ቦረና፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ፋፌን፣ ኤረር፣ ነጎብ፣ ሲቲ፣ ጃረር፣ ቆራሂ እና ዳዋ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት	• የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም • ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት	• ከፍተኛ ትነት መኖር •	• የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል • የደረሱ የበልግ ሰብሎችን የሚኖሩ ደረቅ ቀናቶች በመጠቀም መሰብሰብ

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

2.6 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣይ የጁላይ ሁለተኛ አስር ቀናት በአብዛኛው ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል። እንዲሁም አልፎ አልፎ ከሚኖረው ተደጋጋሚ የሆነ ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ተፋሰሶች እንዲሁም የከተማም ሆነ የገጠር አካባቢዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ፣ የወንዞች ከፍታ መጨመር ሊያስከትል ይችላል። በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት ሊኖር የሚችለው አደጋ ለመቀነስም ሆነ መልካም ዕድሎችን ለመጠቀም የሚከተሉትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

የውኃ ተፋሰሶች	የእርጥበት ሁኔታ	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ
በአብዛኛው • ተከዜ • መረብጋሽ • አባይ • ባሮ አኮቦ • የላይኛው እና የመካከለኛ • ኦሞ ጊቤ • ስምጥ ሸለቆ አዋሽ	ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት	• የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋን መጨመር • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መሻሻል • የከርሰ ምድር የውኃ መጠን መሻሻል • የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦች ውኃ መጠን መሻሻል	• ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የቅፅበታዊ ጎርፍ ስጋት መጨመር • የወንዞች ከልካቸው በላይ መሙላት • የደለል ስጋት መጨመር • በከተሞች አከባቢ ከሚኖረው ዝናብ በመነሳት የትራፊክ መጨናነቅ መፈጠር	• የጎርፈ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት • ወራጅ ውኃን በእግርም ሆነ በቀላል ተሽከርካሪ ለማቋረጥ አለመሞከር • የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም • የጎርፍ ተጽዕኖ ትንበያዎችንና ምክረ ሀሳቦችን በየጊዜው መከታተል • የጎርፍ የፍሳሽ መውረጃዎች ቦዮችን ማፅዳት
በአብዛኛው የመካከለኛው እና የታችኛው • አዋሽ	ከመጠነኛ እስክ ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ	• የጎርፍም ሆነ የደለል ስጋት አለመኖር	• ዝቅተኛ የውኃ ፍሰት • እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች የውሃ እጥረት	• የውኃ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

• አፋር ደናክል • ገናሌ ደዋ • ዋቤሸበሌ ኦጋዴን			• ከፍተኛ ትነት	• የሚገኘውን የዝናበ ውኃ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል • ከጣራ እና ከመሬት ወለል የዝናብ ውኃን በተግቢ ሁኔታ ማሰባሰብ • የውኃ እጥረት በሚገጥማችው አካባቢዎች የውኃ ተደራሽነትን ማረጋገጥ

Ethiopian Meteorology Institute

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et